# ከእንግዲህ እነዚያኑ ተቃዋሚዎች
# እምነን እንታገል
# ወይስ
# አዲስ ጠንካራ ፓርቲ እንፍጠር ?

*ከአስተዋይ በቀለ*

ለኢትዮጵያ የሚቆረቆረው ኃይል በየቦታውና በየሁኔታው በገሃድም፣ በሚስጢርም እየተወያየበትና እየተመካከረበት ያለው ጉዳይ በአርስቱ ላይ የተመለከተው ወቅታዊ የፖለቲካ ጥያቄ አለው።

በፖለቲካ ስትራቴጂ አንፃር የፖለቲካ ወሮበልነትና ቅሌት ከዋጠው መላቅጡን ካጣ፣ ፍሬ አልባ ተቃውሞና ድርጅታዊ ድክመት መላቀቅ አለመቻል ትልቅ ታሪካዊ ስህተት ነው። ይህን የማይገነዘቡ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና ደጋፊዎቻቸው ሁሉ አገሪቷንና ሕዝቡን እየጎዱ መሆኑን ማወቅ አለብን።

- የትኛው ድርጅት ነው ከወያኔ የበለጠ ወይም አቻ የሆነ የፖለቲካ ፓርቲ፣ አባላትና አሰራር ያለው?

- የትኛው ድርጅት ነው ከመነሻው ጀምሮ እድገት እያሳየ፣ ሕዝብን በብዛት እያቀፈ፣ አገራቱን እያዳረሰ፣ በሂስና ግለሂስ ራሱን እያጠራና እያጠናከረ የመጣው?

- የትኛው ድርጅት ነው ከገንዘብ አንፃር እንኳን አስተማማኝ ምንጭ አደራጅቶ አዋጡልኝ ከማለት ልመና ራሱን ያዳነ?

- እስቲ ንገሩን ከወቅቱ አንፃር የትኛው ተቃዋሚ ድርጅት ነው የወጣት ኃይል እንቲፍዳ ማቀጣጠልና ሰላማዊ ሕዝባዊ አመጽ ማነሳሳትና ማጋየት የሚችለው?

- የትኛው ድርጅት ነው በኢትዮጵያ፣ በሕዝቦቿና በብሔራዊ ጥቅሞቿ ላይ ከወያኔ የተለየ ጥርት ያለ የፖለቲካ አቋምና መስመር ያለው?

- የትኛው ድርጅት ነው መስዋዕትና በመስዋዕትም ላይ መስዋዕትነትን ደርቦ ለመክፈል ቆራጥነትና የትግል ፅናት ያላቸው አባላትን በብዛት በውጭና በአገር ውስጥ ያደረጀና የሚያንቀሳቅስ?

- የትኛው ድርጅት ነው ራሱን፣ አባላቱንና ደጋፊዎቹን ከወያኔና ከሌሎችም ኃይሎች ሴራና ጥቃት ለመከላከል የሚያስችል ሰፊ የፕሮፓጋንዳና ኢንተሌጀንስ ተቋም፣ አደረጃጀትና እንቅስቃሴ ያለው?

- የትኛው ድርጅት ነው ለኢትዮጵያ በጐ አስተያየት ባላቸው መንግሥታት ዘንድ ተቀባይነት፣ ሁሉ-ገብ ድጋፍና እርዳታ ያገኘ?

- የትኛው ድርጅት ነው በአገር ውስጥና በውጭ ያሉትን ተቃዋሚ ፓርቲዎች በሰመረ ኅብረት፣ በማዕከላዊ አመራርና ለትግል አንድነት በማብቃት፣ ተቀባይነት ተሰሚነትና ተከታይነት ያለው?

- የትኛው ድርጅት ነው በየረድፉ፣ በየሙያው ያሉ የኢትዮጵያን ምርጥ ልጆች ሰፊ ያገርና የመንግሥት ልምድ ያላቸውን የፖለቲካ ባለሙያዎች አሰባስቦ ያቀፈና የሚያሰራ?

- የትኛው ድርጅት ነው ለምሳሌ፣ "ልዋጭ- ልዋጭ" እያለ መሃል ገብቶ አገሪቷንና ሕዝቧን የሚቃኝና በወያኔ መንግሥታዊ ተቋማት ውስጥ የራሱን ሰዎች በሚስጢር አስርጎ የሚያሰራና ለነገው ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ቁጥጥር አበክሮ የሚዘጋጅ?

**ወዘተ**

እስከዛሬዎቹ የፖለቲካ ተቃዋሚዎች ጋር ከእንግዲህ አብሮ መጓዝ እስካሁን የትም አላደረሰንም። ዛሬም- ነገም የትም አያደርሰንም። ሽንፈት በሽንፈት ላይ መከናነብ ካልሆነ በስተቀር።

በማንኛውም እረድፍ ብቃትና ቆራጥነት ከሌላቸው ድርጅቶች ጋር ከመጓዝ ይልቅ ለምን በድርጅታዊ አወቃቀሩና ፅናቱ፣ በአባላቱ ስብጥርነት፣ በሕዝባዊነቱ፣ በአገር ወዳድነቱ፣ በአመራር ስልቱ፣ በማይታጠፍ ትግሉ፣ በቆራጥ መስዋዕትነት ከፋይነቱ፣ ብቃትና ክሬድንሻል ያለው ሃቀኛ አዲስ ግዙፍ ፓርቲ አናደራጅም? የሚለው ጥያቄ እየጎላና ተቀባይነት እያገኘ ነው።

ኢትዮጵያ ሕዝቧን እናድን ካልንና ከልብ ከቆረጥን ወደር የማይገኝለት እንደ ንሥር አሞራ በአሸናፊነት ነጥቆ የሚወጣ አውራና ሁነኛ በፍጥነት በመፍጠር በአገር ውስጥና በውጭ አገር መደራጀት አለበት።